# ሰሞኑን በፓል ቶክ
# ቁጥር አራት
# አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል።

ከበልጅግ አሊ

ሰሞኑን የ"ንፁህ ኢትዮጵያዊነት" ሹመት በደደቦች ሸንጎ የተነፈገ አንድ ሰው ሲሆን እሱም የኢንጅነር ሃይሉ ልጅ አንተነህ ሃይሉ ነው። ሌላው በደደቦች ሸንጎ ባስቀመጥኩት የደደቦች ስድብ መለኪያ ኢሕአፓ ከነበረበት የአንደኝነት ቦታ ወርዶአል ። ቦታውን ዶክተር ታዬ አለተቃዋሚ ወስዶታአል። በሁለተኛም ደረጃ አንተነህ ሃይሉና ኢሕአፓ ይፈራረቃሉ።በሶሰተኛ ደረጃ የደደቦች ሸንጎና በኤርትራ የሚገኙ "ነፃ አውጭዎቻችንን" የነ ሙሴ ግሩብ በአሁኑ ግዜ በአላማ ሳይሆን በተሰበሰበ ገንዘብ ተጣለተዋል።ደደቦቹ „የማናውቀውን“ ነገር ሊያስረዱን ይሞክራሉ መሰለኝ።ይኸውም እነ ሙሴ ለሻቢያ ነው የሚሰሩት እያሉ ይነግሩናል።እኛን ትተው እነርሱ ቆይተውም ከገባቸው ነገሩ አይከፋም ነበር።ነገር ግን እራሳቸው ደደቦቹ ወደ ኤርትራ ደጅ ለመጥናት መልዕክተኛ ለመላክ ከፍተኛ ጥረት ላይ ናቸው። እንደሚሉት ከሆነ የኤርትራ መንግስት የነርሱን ሃሳብ ካልተቀበለ ጉዱን ነው እንደሚያፈሉት ነው።እኔ በበኩሌ ሻቢያ በደደቦቹ ጉዱ ሲፈላበት ለማየት በናፍቆት ነው የምጠብቀው።

ከዚህ በተረፈ በፓልቶክ የደደቦች ሸንጎና እነ ፕሮፌሰር ሙሴ ከተለያዩ በኋላ አንዳንድ ሚስጥር ከኤርትራ እየወጣ ነው።ይኸውም በኤርትራ ውስጥ የታሰሩ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ ነው።ይህ ሚስጥር ከተከፋፈሉ በኋላ የወጣ ሲሆን ሳይከፋፈሉ የታሰሩትም ሆነ የተገደሉ እንዳሉ የሚታወቅ ነገር የለም።

ከነዚህ በኤርትራ በሚገኙት ተቃዎሚዎች ጋር ሕብረት የፈጠሩ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች (ይህ ቅንጅትንም ይመለከታል) የታሰሩትን ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት ምንም አይነት እስከ አሁን የወጣ የተቃውሞ መግለጫ የለም። ዛሬ ለኢትዮጵያውያን መብት ቆምን የሚለውን ተቃዎሚዎች እንዲያውም ከእነዚህ ኢትዮጵያውን አስረው ከሚያሰቃዩ ድርጅቶች ጋር ህብረት ፈጥረው ሌሎች ስለእስረኞቹ የሚታገሉትን ድርጅቶች ሲወጉ ይታያሉ።ለዚህ በኤርትራ መንግሰት ቁጥጥር ስር ላለ ህብረት ተብሎ የኢትዮጵያውያንን ስቃይ ዝም ብሎ ማለፍ ተገቢ አደለም። ለኔ የቅንጀት መሪዎች ይፈቱ ከሚለው እኩል በኤርትራ ውስጥ እውነቱን ከአወቁ በኋላ ስለተቃወሙ የታሰሩ፣የተገደሉ፣ የተገረፉ ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ያሳስበኛል። በምናደርገው ማንኛውም ስልፍና ተቃውሞ የነዚህን የምስኪኖች ስም ልናነሳ ይገባል። ወይንም እንደተለመደው ማስረጃ የለንምና ይህንን ጥያቄ አናነሳም እንደተባለው እንደን ደብተራው ጉዳይ የተወሰኑ የፓለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ ሆኖ ሊቀርም አይገባም።

በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔዎች ስብስብ አንድ የፓልቶክ ክፍል በሲቪሊቲ ስም አቋቁሞል።ሰሞኑን ከሁሉ የሚገርመው ይህ ክፍል የህግ የበላይነትን እንዲያስረዳ የቀድሞውን የደርግ አባል ፣ የመላኩ ተፈራን የቅርብ ጓደኛ ፣ በመንግስቱ ሃይለማርያም ስም በተከፈተው ክስ ተከላካይ ጠበቃ ፣ ባንዳ ሞላ ዘገዬ ስለ ሕግ የበላይነት ቃለ መጠይቅ ጋብዞ ነበር።ይህ ግለሰብ በጣም ተዎቂነቱ በፀረ ኢሕአፓ አቋሙና ፋሽሽታዊ አመለካከቱ ሲሆን አሁንም ለኢሕአፓ አባላት ከቀይ ሽብር ሌላ የሚመኘው እንደሌለ የታወቀ ስለሆነ የወያኔዎችን አድናቆት አትርፎለታል። በዚህም ምክንያት በብዙ የወያኔ ሚዲያዎች ላይ በተደጋጋሚ ሲቀርብ ነው የከረመው።ለኔ ከዚህ „ ዴሞክራት“ የደርግ አባል ሌላ ወያኔ ሊያቀርበው የሚችለው ምንም የሚመስለው ግለሰብ አያገኝም። በሰባዊ መብት ጉዳይ ደርግና ወያኔ ተመሳሳይነት ስላላቸው እርስ በራስቸው ሊማማሩ ይችላሉ።ከባንዳ ሞላ ዘገዬ ወያኔ ስለ ቀይ ሽብር፣ ስላፈና፣ ወያኔ ከሚያውቀው

በተጨማሪ ገለፃ ሊያገኝ ይችላል። ከዛ በተረፈ ግን ባንዳ ሞላ ዘገዬ የህግ የበላይነትን ስለማያውቀው ለማንም ሊያስረዳ አይችልም።

የወያኔው ክፍል አጋፋሪዎች ተከፍሎአቸው የሚሰሩ የወያኔ ፕሮፓጋንዲስቶች ሆነው ነው ያገኘኋቸው።ሌሎቹ የወያኔ አባላት ከፍለው የሚያሰሩትን ለመቆጣጥ የመጡ ይመስል በክፍሉ ውስጥ ቢታደሙም ብዙም አይሳተፉም።አንዳንድ የዋህ የሆኑ የሌላ ክፍል አባላት ከመጡ ደግሞ እንደሁኔታው እየታዬ የወያኔን የመከፋፈያ ሴራ እንዲሰሙ ይጋበዛሉ ።ይህም ማለት ኢሕአፓን ለሚጠላው ኢሕአፓን በማጥላላት ፣ ደርግን ለሚጠላው ኢሰፓን በማጥላላት ወደ „ወያኔ ይሻላል“ ወደ የሚለው ቲወሪ ሊወስዱዋቸው ጥረት ያደርጋሉ። የተቃዎሚው ክፍል በምን እንደተከፋፈለ ስለሚያውቁ ያንን በመጠቀም መከፋፈሉን እዚህ እራሳቸው ክፍል በግለፅ ሲያኪያሂዱት ይታያሉ።በሌላው ክፍል ደግሞ በሰርጎ ገቦቻቸው በመጠቀም የተቃዎሚዎች ጎራ ሲከፋፍሉ ነው የሚውሉት።

ይህ ክፍል እንደ ፖለቲካ ድርጅትም ወይም እንደ መደበኛ ስብሰባ ያደርገዋል። ኤርትራን በሚመለከት የአቋም መግለጫም አውጥቶ በአይጋ ፎረም ላይ ለጥፎአል።ወጣ ገባ በሚለው ተሳታፊ ነው የአቋም መግለጫ የሚወጣው? የቸገረው እርጉዝ ያገባል ማለት ይህ ነው።

ይህ ክፍልም ሆነ ሌሎች የወያኔ ሜድያዎች የማይሞክሩት ነገር እንደሌለ የሚታይ ሃቅ ነው። ዛሬ ሶስተኛ ካርታቸውን አውጥተው ይገኛሉ።

1ኛ.በሶማሌ ጣልቃ ገብነት እናገኘዋለን ያሉት የህዝብ ድጋፍ ፉርሽ ሆኖአል።

2ኛ.የሚሊየንም ዝግጅትም እየተንኮዳኮደ ነው ።

3ኛ.አሁን ሶስተኛውን ካርታቸውን ስበዋል።

ይህም ከኤርትራ ጋር በሽብርተኝነት ስም አንዳንድ ሁኔታዎችን መፍጠርና የአንዳንድ የዋሆችን ድጋፍ ማግኘትና በአሁኑ ግዜ ከምርጫው በኋላ የተፈጠረባቸውን የፖለቲካ ቀውስ በሌላ ትኩስ ዜና ለመቀየር የሚደረግ ጥረት ነው።ይህንን የሚቀጥለው የወያኔ ተንኮል መሆኑን ልንገነዘበው ይገባል። የሚገርመው የወያኔ ሚዲያዎች የተቃዋሚ ድርጅቶች የሚሉትን ወስደው ሻቢያ ለሃገራችን የሞቶ አመት የቤት ስራ ሊሰጣት ነው ሲሉ ይደመጣሉ ። እነርሱን ያልገባቸው ግን ወያኔ እራሱ ሻቢያ ከሚለው የመቶ አመት የቤት ስራ ውስጥ አንዱ መሆኑን ነው።ሶስተኛውን የወያኔ ካርታ በሚመለከት ወደፊት በሰፊው እመጣበታለሁ።

ሌላው በፓልቶክ እየበዛ የመጣ ነገር የኢሕአፓ አባል ነበርኩ የሚለው የኢሰፓ አባላት ቁጥር እየጨመረ መጥቶል።የክፍሉ ታደሰን መፀሀፍ ያነበበ ሁሉ ስለ ኢሕአፓ ሁሉን ነገር የሚያውቅ ይመስለዋል።ያም ታላቅ ስህተት ላይ እየጣላቸው ነው። ባለፈው ሳምንት አንድ የኢሰፓ አባል መሆኑ ከሚጠቀመው ቋንቋ ወዲያው ለማወቅ የሚያስችል ግለሰብ የኢህአፓ አባል ነበርኩ ብሎ የሰጠን የምስክርነት ቃል እስከ አሁን ብዙዎቻችንን ሲያስቀን ግለሰቡን በግል ስለማውቀው እኔን ደግሞ በተለይ ፍንድት ብዬ እንድስቅ አድርጓኛል።ግለሰቡ እንደሚለው ኢሕአፓን ሲቀላቀል ገና የአስራ አራት አመት ጉብል ነው። ከዛም በቀይ ሽብር ከአንድ የኢሕአፓ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ተጠቁሞበት ብዙ እንደተሰቃዬ ነው ያወራን።ጉድ እኮ ነው የአስራአራቱ አመት የኢሕአፓ አባል በማእከላዊ ኮሚቴ አባል ሲጋለጥ። ዋናው የቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል መሆኑን አለማወቁ ነው። ምን ችግሮት መፀሐፉን በደንብ አላነበበውም እንጂ እንደ ማናቸውም ውሸታም ሰው ምስክርነት የሞተ ሰው ቢጠራ ይችል ነበር። ከተሰውት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባለት መካከል አንዱን ለምስክርነት ቢጠራ ይሻለው ነበር።

በመጨረሻም አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል እንዲሉ ወያኔ በየፓል ቶኩ ያመጣቸው ጮሌ ፕሮፖጋንዲስቶች በባዶ ሜዳ የበለፀገች አገር ወይም የዴሞክራሲ ምሳሌ አደርገው ቅስቀሳ ቢያደርጉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወያኔ ያሳየውን ጥላቻ በሰላ ምላስ ብቻ መለወጥ አይቻልም። እሰርቤቱ በፖለቲካ እስረኞች ሞልቶ የህግ የበላይነትን ባንዳ ሞላ ዘገዬ ሊያስረዳን አይችልም። የደደቦች ሽንጎም ሻቢያን ደጅ ለመጥናት የሚያደረጉት ጥረት ዋጋ እንደሌለው አውቀው የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል።

በሁሉም አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ !!!!

በልጅግ አሊ